# ግ ል ጽ ደ ብ ዳ ቤ

ለአቶ መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር
አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

ክቡር አቶ መለስ

ኢትዮጵያን በመሳሪያ ሀይል ይዘው ስልጣን ከጨበጡበት ጊዜ ጀምሮ እንደወቀስ ኩዎት እንደአሰለቸሆት ብገነዘብም ይህንን ደብዳቤ ለመጨረሻ ጊዜ ልጽፍልዎ ተገደድኩ፡ የዛሬው መልእክቴ ቃሊቲ እስር ቤት አስረው በቀጠሮ ስለሚሰቃተዩት ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ድርጅት መሪዎች ነው።

ከእስረኞቹ አንደኛው ዶክተር ያእቆብ ሀይለ ማርያም በራሳቸውና በታሰሩት ጓደ ኞቻቸው ስም በጥር ወር 1999 አመተ ምህረት ግልጽ ደብዳቤ፤ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለክቡራን ዳኞች በማለት የጻፉት ደብዳቤ በኢንተርኔት በመላ አለም ስለተሰራጨ፤ እርስዎ ለማንበብ ጊዜ ባይኖርዎትም፤ ጉዳዩ እርስዎን በተመለከተ ስለሆነ የስራ ባልደረቦችዎ ሳያቀርብልዎት አይቀሩም። ዶክተር ያእቆብ ስለክሱ ፕሮፌሶር መስፍን ወልደ ማርያምን በመጥቀስ « በመንግስትና በእኛ በተከሳሾቹ መሀል ያለው ያለመግባባት በውይይትና በመግባባት ሊፈታ የሚችል ፖለቲካዊ ጥያቄ እንጂ የወንጀል ጉዳይ አለመሆኑን በአጽንኦት አሳስበው ነበር ይሉና ፤ ዶክተር ያእቆብ ጽሁፋቸውን በመቀጠል፤ በጉዳዩ አስተያየታቸውን የሰጡ አለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጅትና አንዳንድ የአገር መሪዎችም ጭምር አለመግባባቱ ፖለቲካዊ መሆኑን አሳስበው በውይይትና በመግባባት እንዲፈታ በብዙ ተማጽነዋል ተከሳሾችም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲለቀቁ እነሆ ተማጽኖአቸውን እስከዛሬ አላቋረጡም። ብዙ ኢትዮጵያውያንም አለመግባባቱ የወንድማማችና የእህትማማች እንደመሆኑ መጠን የቂምና የቁርሾ ጠባሳ በሚተው በህግ እሰጣ አገባ ሳይሆን በውይይት መፍትሄ ይሰጠው ዘንድ መንግስትን ለማሳመን ብዙ ጥረዋል »

ዶክተር ያእቆብ ከዚህ በፊት የደረሰውን ፍርድ በመጥቀስ ፡ በአገራችን በተለያዩ ጊዜያት በወቅቱ የነበረውን ስርአት እንለውጣለን በማለት የተነሱ አገር ወዳዶች ላይ ክሶች ተመስርተው ትልልቅ ፍርዶች ተበይነዋል፤ በእነ በላይ ዘለቀና በጀነራል መንግስቱ ንዋይ፤ በጀነራል ታደሰ ብሩና፤ በኮ/ል አለሙ ቂጢሳ ላይ የተመሰረቱት ኢፍትሀዊ ፍርዶችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ይህ ከፊታችን ያለው ፍርድ ግን በሀገራችን ፍትህ ላይ ከኢኮኖሚው ተጽእኖ በአገራችን ሰላም ልማትና ዴሞክራሲ ከማቅጨጭ ወይንም ከማጎልበት አንጻር በጠቅላላው ፍርዱ በአገራችን መጻኢ እድል ላይ ከኤኮኖሚው ጣና ሲታይ ከዚህ ቀደም በአገራችን ከተካሄዱት ክሶችና ፍርዶች ሁሉ የተለየና የላቀ ነው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። በዚህ ጉዳይ ላይ ፍርድ በሚሰጥበት ወቅትም የኢትዮጵያውያንና የመላው አለም ህዝብ አይንና ቀልብ በዚች ትንሽ ከተማ በምትገኝ ፍርድ ቤት ላይ ያተኮረ እንደሚሆን አልጠራጠርም።

ዶክተር ያእቆብ በጽሁፋቸው ወረድ ይሉና፤ የጀነራል መንግስቱ ንዋይ የእነ ሀይለ ስላሴን መንግስት አስወግደው ስርአቱን ለመለወጥ የነበራቸው ራእይ ሳይሳካ ቀርቶ በአገር ክህደት ወንጀል ተከሰው ፍርድ ቤት ቀርበው የተናገሩት ለእኛም አግባብነት አለው፤ ጀነራሉ ለምን የሀይለ ስላሴን መንግስት ለማስወገድ እንደፈለጉ ጉድለታቸውስ ምን ነበር ተብለው በተጠየቁ ጊዜ የሰጡት መልስ እንዲህ የሚል ነበር፤ እኔ ብፈልግ በየቀኑ መኪና መቀያየር እችል ነበር። ብፈልግም ምርጥ የአውሮፓ ሻምፖኝ ልጎነጭ አቅሙ ነበረኝ፤ ሰው ቤተመንግስት ለመግባት ሲከለከል እኔ ከልካይ አልነበረኝም፤ ይህንን ሁሉ ይቅርብኝ ብዬ አገሬን ካለችበት ድቅድቅ ጨለማና ውርደት ለማውጣት ነበር የተነሳሁት። ዛሬ አንዳንድ የቅንጅት መሪዎች ይህንኑ የጀነራል መንግስቱን ቃል በዚህ ችሎት ይደጋግሙት ነበር።

ክቡር አቶ መለስ፤ ዶክተር ያእቆብ የጻፉትን ግልጽ ደብዳቤ ከፊሉን ቃል በቃል ደግሜ የጻፍኩልዎ ያለምክንያት አይደለም፤ የርስዎ ታሪክ ከእርስዎ በፊት ከነበሩት

መሪዎች ጋር የሚመሳሰል ስለሆነ በጋራ እንድንወያይበት በማሰብ ነው፤ ተከሳሾች እን ደገለጹት፤ በሀገራችን ለፍትህ መሚገት ለሰላም መቆም ለነጻነት መታገል በእስርና በሞት የሚያስቀጣ ከሆነ እንደከሱ ጥፋተኞች ነን፤ ሞትንም ሆነ እስራትን በጸጋ እንቀበላለን፤ ክሱን ላለመከላከል መርጠናል ይላሉ። ተከሳሾቹ ወንጀል እንዳልሰሩ ቢያውቁም በእርስዎ መንግስት ፍትህ እንደሌለ ስለተረዱ እስራትንና ሞትን በጸጋ ለመቀበል ያላቸው ጠንካራ አቋም በእርስዎ ላይ የሚያስፈርድብዎ ስለሆነ ቢያስቡበት ከነገ የታሪክ ፍርድ ለማምለጥ ይችላሉ። ታሪክ ስለሚደጋገም፤ ተከሳሾች ስለመንግስቱ ንዋይ ክስ ስለጠቀሱ እኔሱ በጻፉት ላይ በጥቂቱ እንዳክልበት ይፈቀድልኝ። ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመንግስቱ ላይ ሞት ከፈረደበት በኋላ ይግባኝ ትላለህን ተብሎ ቢጠየቅ አንድ ታሪካዊ ንግግር ተናግሮ ይግባኙን አልፈልግም ሲል « እኔ ከአጼ ሀይለ ስላሴ ድንክ ውሾች ያነሰ ደመወዝ የሚያገኙ ሁለት የተራቡ ወታደሮች አጣልቼ ለማደባደብና አገር ለማፍረስ አለመነሳቴን የሚያረጋግጥልኝ፤ ከእናንተ በትእዛዝ ያገኛችሁትን ፍርድ ለመቀበል ከዚህ መቆሜ ነው፤ እናንተ ዳኞች የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለይግባኝ ተቀብያለሁ፤ ይግባኝ ብዬ ጉዳዩን የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ህዝብ ቢሆን ኖሮ፤ ይግባኝ ለማለት በፈለግሁ ነበር፤ ነገር ግን እንደማይሆን አውቃለሁና የአጼ ሀይለ ስላሴን ፊት ለማየት አልፈቅድም። ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ነጻነትና እርምጃ የተነሳሁ ወንጀለኛ ነኝ እንጂ ላፋጀው የተነሳሁ ወንበዴ አይደለሁም፤ ይህንን ለማድረግ ፊልጌ ቢሆን ኖሮ ማንም የማይወዳደረው ሰራዊትና መሳሪያ ሳላጣ ዛሬ በእናንተ ፊት ለመቆም ባልበቃሁም ነበር፤ ዛሬ ከእናንተ ከዳኞችና የሞት ፍርድ እንድትፈርዱብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ ፍርድ ተቀባዩ የዛሬው ወንጀለኛ የነገ ባለታሪክ ነኝ፤ የእኔ ከጓደኞቼ መካከል ለጊዜው በህይወት መቆየትና ለእናንተ ፍርድ መብቃት የዘመኑን ፍርድ ለመጪው ትውልድ የሚያሳይ ይሆናል ዋ ዋ ዋ ለእናንተና ለገዢዎቻችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ሀሳቤ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሳበት ጊዜ የሚደርስባችሁ መአት የሚያሰቅቅ ይሆናል »

ጀነራል መንግስቱ የሰጠው መግለ ጫና ማስጠንቀቂያ በመጀመሪያ ለዳኞች ቀጥሎም ለንጉስ ሀይለ ስላሴ ነበር ይህ ሁሉ ችግር የመጣባቸው በራሳቸው ጥፋት ስለሆነ ማድረግ የሚገባቸውን በወቅቱ ባለማድረጋቸው፤ በ 1966 የተነሳው የለውጥ ማእበል የንጉሱን ሹማምንትንና ራሳቸውን ንጉሱን ጨምሮ ጠራርጎ ስለወሰደ ንጉሱን ማን እንደገደላቸው የት እንደተቀበሩ እስከዛሬ በትክክል አይታወቅም። ንጉስ ሀይለ ስላሴ በጣም ጨካኝ ነበሩ፤ አብዮቱ ተጀምሮ ከከሸፈ በኋላ ከመሪዎቹ ሶስቱ ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ፤ አቶ ገርማሜ ንዋይ፤ ሻምበል ባዩ ጥላሁን እስከ መጨረሻው ተዋግተው በህይወት እጃቸውን ለመስጠት ስለአልፈለጉ ከጀግናው ቴዎድሮስ እንደተማሩት ራሳቸውን ገለው ሲሞቱ ንጉስ ሀይለ ስላሴ አስከሬናቸውን አደባባይ ሰቅለው መቀጣጫ ካደረጓቸው በኋላ ወደ አልታወቀ ስፍራ እንዲጣል አደረጉ። ጀነራል መንግስቱ ንዋይ ይግባኝ ባይልም በህገ መንግስቱ መሰረት ንጉሱ የሞቱን ፍርድ አጽንተው በተሰቀለበት ጊዜ ጠዋት በልዩ መኪና ተከለ ሀይማኖት ሄደው ከመኪና አውርደው ሲሰቀል ካዩ በኋላ አስከሬኑን የት እንዳደረሱት አይታወቅም፤ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ በድን ስጋው የተከበረ ስለሆነ፤ ክርስቲያን ነኝ የሚሉት ንጉስ ይህንን ለማድረግ ባለመፈለጋቸው የሳቸውም አስከሬን የት እንደተቀበረ አይታወቅም። ወያኔ ከመጣ በኋላ አጽማቸው ቅድስት ስላሴ ተቀበረ ቢባልም የልጅ ልጃቸው ልኡል ኤርሚያስ የሳቸው አጽም አይደለም በማለት በቀብሩ ስነ ስርአት አልተገኘም። በዘመኑ የነበሩት ፓትሪያርክ አቡነ ባስልዮስ ወታደሩ የንጉሱን መንግስት እንዳይወጋ በእግዚአብሄር ስም ሲገዝቱት፤ ንጉሱ አስከሬን ሲሰቅሉ ድምጻቸው አልተሰማም፤ ዛሬ አባ ጳዎሎስ መለስ ዜናዊን ቢደገፉ ያስደንቃል?

ክቡር አቶ መለስ፤ ጀነራል መንግስቱ በንጉሱ መንግስት ትክክለኛ ፍርድ ስለሌለ ይግባኝ አልልም ብሎ እንደተሰቀለው፤ የቅንጅት መሪዎችም በመለስ መንግስት ፍትህ የለም፤ እስራትም ሆነ ሞትን ለመቀበል ዝግጁ ነን ሲሉ በጽሁፍ አስታውቀዋል፤ የርስዎ ውሳኔ ምንድነው? እስከዛሬ እንደ አደረጉት ዳኞችን በመቀያየር በጥቅም በመግዛት በማስፈራራት ይፈርዱባቸዋል ወይስ በነጻ ይለ ቋቸዋል? ጃንሆይ ራሳቸውን ወዳድ ስለሆኑ በመንግስቱ ላይ ሞት ፈርደው፤ መንግስቱ

እንደተነበየው ስጋቸውንና ታሪካቸውን ገለው አለፉ። እርስዎስ አቶ መለስ ምን ይላሉ፤ ብዙ መሪዎች እውተኛ ታሪካቸው የሚጻፈው ከሞቱ በኋላ ሲሆን፤ እርስዎ እድለኛ በመሆንዎ፤በህይወት ለማንበብ ቻሉ። በእሳት ከተፈተነው የትግራይ ወርቅ ህዝብ በመወለድዎ ሲኩሩ አሁን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በሰሩት ግፍና በደል የቂምና የቁርሾ ጠባሳ ትተው ስለሚሄዱ ይህ ችግር እንዳይደርስብዎ በፍጥነት አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ ይገባዎታል። መሪዎቻችን ከታሰሩበት ቀን ጀምሮ በእነሱ ላይ ለመፍረድ ተጨባጭ ማስረጃ ባለማግኘትዎ ምስክሮች በገንዘብ ገዝተው ቢቀርቡም ህሊናቸው ስለአልፈቀደላቸው አገራቸውን ለቀው ኮበለሉ፤ የቀሩትም አቃቤ ህግ ያስጠናቸውን ስለተናገሩ ለእርስዎ ከፍ ያለ ሀፍረት ሆኗል። በዚህ አይነት የውሸት ክስ የሚቀጥሉት እስከመች ድረስ ነው? ብልህ ሰው ከሌላው ስህተት ስለሚማር፤እርስዎ ብልህ ሰው ስለሆኑ፤ ከንጉስ ሀይለ ስላሴና፤ ከመንግቱ ሀይለ ማርያም ስህተት አልተማሩም? ተስፋውን የቆረጠ ህዝብና ከቀፎው የወጣ ንብ መመለሻ ስለሌለው ይህ እርስዎ ለብዙ ለአመታት የሚያሰቃዩት ህዝብ ገንፍሎ ቢነሳ መግቢያዎ የት ነው? ስልጣን ያባልጋል፤ ያሳሳል፤ያስፈራል ያስመካል፤ ዛሬ የሚመኩበት የአሜሪካ መንግስት ከተጠቀመብዎ በኋላ አንድ ቀን እንደሳዳም ሁሴን ሞት ያስፈርድብዎታል። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እንዳለፈው ጊዜ የራሱን ህዝብ ለመፍጀት የርስዎ መሳሪያ ለመሆን አይፈልግም።

ኢትዮጵያ በረጅም ዘመን ታሪኳ የሰው አገር የወረረችበት ጊዜ የለም። በእርስዎ ዘመነ መንግስት ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደር ጎረቤቱን ተኩሶ ገደለ እራሱም ሞተ በማያገባው ጉዳይ ልጆቹን ያለአባት አስቀራቸው። ይህ ሁሉ ጥፋት የመጣው በእርስዎ ምክንያት ስለሆነ ለአሜሪካ ጥቅም የማይጠፋ እሳት አቀጣጥለው ማለፍዎ ያሳዝናል፤ ዛሬ ሱማሊያን በመውጋትዎ፡ እንደጀግና የሚቆጥርዎ ሆዳሞች ነገ እጅዎን አስሮ ለህዝብ ፍርድ የሚያቀርብዎ አሁን የሚተማመኑበት ሆዳም መሆኑን አይዘንጉት።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆነ የቅንጅት መሪዎች ፍላጎት ሰላምና ፍቅር ፍትህንና እኩልነትን እንጂ ቂምና በቀልን ደም መፋሰስን አይፈልግም፤ህዝባችን ብዙ ደም አፍሷል ብዙ እንባ አንብቷል፤በቃ በቃ።በውጭ አገር የሚኖረው በሚሊዮን የሚቆጠረው ስደተኛ በእርስዎ ምክንያት በሰው አገር ተሰዶ በተማረው ትምህርት አገሩንና ህዝቡን ለመርዳት ስለአልቻለ እውቀቱን ጉልበቱን ገንዘቡን ለባእድ ስለሚሸጥ፤ አንድ ብሄራዊ እርቅ ተደርጎ ይቅር ለእግዚአብሄር ብንባባል ብዙ እውቀት ያካበተው ስደተኛ ወደ አገሩ ተመልሶ አገሩን ለመርዳት ይችላል። የርስዎ የመለስ ዜናዊ ሆኑ የኢትዮጳያ ህዝብ የወደፊት እድል የወደቀው ለጊዜው በእርስዎ እጅ ነው፤ይህንን የምለው ለጊዜው መሳሪያ የታጠቀ ሰራዊት ስለአለዎት እንዳለፈው ጊዜ የወጣቶቻችንን ደም እንዲያፈሱ አንፈልግም፤ እንቢታዎ ህዝቡ ሌላ አማራጭ እርምጃ እንዲወስድ ስለሚያስገድደው መጨረሻዎ እጅግ የከፋ ሊሆን ይችላል። ከታህሳስ አብዮት በኋላ የንጉሱ መንግስት ምንም መሻሻል ለማድረግ ስለአልፈለገ፤ በስደት ከምኖርበት አገር ለንጉስ ሀይለ ስላሴ ታህሳስ 20-1958 በጻፍኩላቸው ረጅም ደብዳቤ ያሰፈርኩት መልእክት «ግርማዊነትዎ አመራሩን በሰላም ካለወጡ፤ ህዝቡ ተስፋ በመቁረጥ ስለሚያምጽ፤ ደም ቢፋሰስ ምን ይጠቀማሉ? አሁን ያለዎት አማራጭ ስጋዎንና ታሪክዎን ገለው ለትውልዶችዎ የደም በቀል ትተው ማለፍ፤ ወይም ለግል ስልጣን ያለዎትን፤ ጉጉትና ምኞት ወደጎን ትተው በሰላም መንገድ፤ ስልጣኑን ለህዝቡ መስጠት እራሱን እንዲመራ ማድረግ ስለሆነ ምርጫዎን ያሳምሩ» ንጉሱ ደብዳቤዬን ካነበቡ በኋላ «ሟርተኛ« ብለው ቢቆጡም የተፈራው ደረሰባቸው፤ ለሰው ብሎ ሲያማ ለእኔ ብለህ ስማ የሚባለውን የአበው ምሳሌ አቶ መለስ ያውቃሉ ? ማናቸውንም ነገር በሰላም ለመጨረስ የካቲት 12 ቀን በሚደረገው ችሎት አቶ መለስ የቅንጅት መሪዎች በነጻ መለቀቃቸውን፤ አንድ ታላቅ ብሄራዊ እርቅ እንደሚያደርጉ ምስራቹን እንዲያበስሩን በጉጉት እንጠብቃለን። አምላክ ኢትዮጵያን ይጠብቃት።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ፍራንክፉርት፤ ጥር 24.1999 (01.02.07) ጌታቸው ጋረደው



" እኔ ከአፄ ኃይለሥላሴ ድንክ ውሾች ያነሰ ደመወዝ የሚያገኙ ሁለት የተራቡ ወታደሮች አጣልቼ ለማደባደብና አገር ለማፍረስ አለመነሳቴን የሚያረጋግጥልኝ ከእናንት በትዕዛዝ ያገኛችሁትን ፍርድ ለመቀበል ከዚህ መቆሜ ነው። እናንተ ዳኞች የበየናችሁብኝን የሞት ፍርድ ያለይግባኝ ተቀብያለሁ። ይግባኝ ብዬ ጉዳዬን የሚመለከትልኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ ይግባኝ ለማለት በፈለግሁ ነበር። ነገር ግን እንደማይሆን አውቃለሁና የአፄ ኃይለሥላሴን ፊት ለማየት አልፈቅድም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ነፃነትና እርምጃ የተነሳሁ ወንጀለኛ ነኝ እንጂ ላፋጀው የተነሳሁ ወንበዴ አይደለሁም። ይህንን ለማድረግ ፈልጌ ቢሆን ኖሮ ማንም የማይወዳደረው ሠዊትና መሳሪያ ሳላጣ ዛሬ በእናንተ ፊት ለመቆም ባልበቃሁ ነበር። ከናንተ ከዳኞችና የሞት ፍርድ እንድትበይኑብኝ ካዘዛችሁ ሰው ይልቅ ፍርድ ተቀባዩ የዛሬው ወንጀለኛ የነገው ባለታሪክ ነኝ። የእኔ ከጓደኞቼ መካከል ለጊዜው በሕይወቴ መቆየትና ለእናንተ ፍርድ መብቃት የዘመኑን ፍርድ ለመጪው ትውልድ የሚያሳይ ይሆናል። ዋ! ዋ! ዋ! ለእናንተና ለገገር.ዎቻችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀሳቤ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሳበት ጊዜ የሚደርስባችሁ መአት የሚያሰቅቅ ይሆናል??"

ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ
መጋቢት 19 ቀን 1953

60 የሚሆኑትን ያለፍርድ ስለረሸኑ የስዊስ መንግሥት ከነፍሰ ገዳዮች ጋር አልነጋገርም በማለት ጉዳዩ ፋይዳ አጥቶ ቀረ::

**አርማችን፤** ንጉሡ ከሥልጣን ከወረዱ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ አላሰቡም ውይንምአልሄዱም?

**አቶ ጌታቸው፤** ንጉሡ እሥር ቤት በነበሩበት ወቅት ለሦስት ሳምንት ወደ ሀገሬ /ኢትዮጵያ/ ሄጄ ነበር:: ግን ሥራ ስለምንሰጥህ ከቤተ መንግሥት እንዳትርቅ ስለተባልኩ ለሁለት ሳምንታት ከታች ግቢ አልጠፋሁም:: እኔ የሥራ ፍላጎትም ችግርም ስለ አልነበረኝና ሁኔታውም ስለ አላማረኝ ተመልሼ እመጣለሁ በማለት የመቶ ሺህ ብር ዋስ ጠርቼ ወደ ጀርመን ተመለስኩ::

**አርማችን፤** በአገራችን ውስጥ እስከ ዛሬ ከተካሄዱት

**አርማችን፤** የዛሬውን የአንድ ጎሳ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝስ እንዴት ይገመግሙታል? መጨረሻቸውስ ምን ሊሆን ይችላል ብለው ያስባሉ?

**አቶ ጌታቸው፤** እነዚህ የበረሃ ሽፍቶች አጥፍተው ለመጥፋት የመጡ ስለሆነ ጊዜውን ለመተንበይ ባይቻልም ተሎ ጠፊዎች ናቸው:: ሕዝባችን በደርግ አገዛዝ ላይ የነበረውን ጥላቻ በመጠቀም ምኒልክ ቤተ-መንግሥት ከገቡ ጊዜ ጀምሮ የሚሠሩት ግፍና በደል ሕዝቡ እንዲያምፅ የሚያስገድድ ቢሆንም ሕዝባችን በትግሥት ሁሉን ችሎ በመቀመጡ ወያኔዎች እንደፍርሃት በመቁጠር በማንአለብኝነት የፈለጉትን ለማድረግ የልብ ልብ ተሰምቷቸዋል:: በሁሉም መስክ የትኩረት አቅጣጫቸው ወደ ትግራይ ብቻ በመሆኑ ለቀሪው ክ/ሀገር ልማት ማሰብ ቀርቶ የነበረውን



"እነዚህ አጠና እንጨት ላይ የተሰቀሉት ሦስት ዜጎች ኮ/ል ወርቅነህ ገበየሁ፥ ገርማሜ ንዋይ፥ ሻምበል ባዬ ጥላሁን ለሕዝባቸው ሰበዓዊ መብትና እውነተኛ ነፃነት እስከመጨረሻ ታግለው እጃቸውን ለጠላት ከመስጠት በአገራቸው ባህልራሳቸውን ከገደሉ በኋላ በኃይለሥላሴ ትዕዛዝ አስከሬቸው በአደባባይ ተሰቀለ:: መንግሥቱ ኃይለማርያም በንጉሡ ላይ የፈጸመውን የግፍ አገዳደል ከአወገዝን የንጉሡን ኢሰበዓዊ አድራጎት እንደግፋለን ወይስ እንቃወማለን? ሰው ክቡር ፍጡር ስለሆነ አስከሬኑ ይቀበራል እንጂ አደባባይ ላይ ስቅሎ መቀጣጫ ማድረግ ከአውሬ አለመሻል ነው:: አስከሬን መስቀል የሞተን መውቀስ የሰማነውና ያየነው በኃይለሥላሴና በመለስ ዜናዊ ዘመነ መንግሥት ነው:: አምላክ ታጋሽ ቢሆንም ጊዜውን ጠብቆ በሰፈሩት ቁና መስፈሩ የእጅን ዋጋ ማስከፈሉ ስለማይቀር በሕይወት ያለነው ከዚህ ስህተት ብንማር ከነገ የታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን እንችላለን::"

ለውጦች የተደሰቱበትና የደገፉት አለን?

**አቶ ጌታቸው፤** እኔ እስከማውቀው ድረስ የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለማስወገድ ብዙ ሙከራዎች ሲከሽፉ፥ ያለ ደም መፋሰስ ስልጣኑን የተቆጣጠሩት የደርግ መኮንኖች ስለነበሩ ተደስቸባቸዋለሁ:: የሞራል ድጋፍም ሰጥቻለሁ:: ግን ፀጥታውን አስከብረን ሥልጣን ለሕዝብ እናስረክባለን ያሉትን ቃል ለውጠው ለራሳቸው ጥቅምና ሥልጣን ብቻ ስለ ተሯሯጡ፥ ያለደም መፋሰስ የጀመሩትን ንቅናቄ የደም ጎርፍ ስለአደረጉት ከስልጣን እስከተባረሩበት ጊዜ ድረስ ተቃውሞዬን ስገልጽ ቆይቻለሁ:: ጥይት ባልተኩስባቸውም መጨረሻቸው እንደ አፄ ኃይለ ሥላሴ እንደሚሆን ደጋግሜ አሳስቤያቸዋለሁ::

በመዝጋትና እየነቃቀሉ ወደ ትግራይ በማጓጓዛቸው ሕብረተሰቡ ለተለያዩ በሽታ ከመጋለጡም በላይ በከፋ ረሃብ ምክንያት እንደ ቅጠል ረግፏል :: ከዚህ እኩይ ድርጊታቸው እንደምንረዳው ወያኔዎች የኢትጵያን ሀብት እንጂ ሕዝቡን እንደ ማይፈልጉት ነው:: ያላቸው የረጅም ጊዜ ዕቅድ አንድ ቀን ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥለው የራሳቸውን መንግሥት ለማቋቋም ስለሆነ የምግብ እጥረት እንዳያጋጥማቸው ከጎንደርና ከወሎ ሰሜን ክፍል ወደ ትግራይ አካለውታል:: የጥሬ ዕቃ ችግር እንዳይገጥማቸው ደግሞ የመሃል አገሩን በአቅራቢነት ደረጃ ብቻ እንዲወሰን እያመቻቹት ነው:: ሕዝቡ የራሱን ጥሬ ዕቃ ለራሱ የኢንዱስትሪ ምርት እንዳይገለገል በነፃ ገበያ ስም የአገሪቱን የማምረቻ ተቋሞች በሙሉ በተለያየ

መጠሪያ በሚታወቁ የወያኔ የንግድ ድርጅቶች በሞፖሊ በመያዝ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መስኩን በሙሉ በመቆጣጠር አገሪቷንና ሕዝቡን በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: ብዙኀኑን ሃምሳ ሰባት ሚሊዮን ሕዝብ በቀሪው ሦስት ሚሊን በማይሞላ አናሳ ጎሳ ብቻ ተገዥ ሆኖ እንዲቆይ ማድረግ ይሻሉ::

መጨረሻቸው ምን ይሆናል ለሚለው ጥያቄ እነዚህ በጠመንጃ ኃይል ለሥልጣን የበቁ ጥቂት ወንበዴዎች እንኳን መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ



"አንድ ቀን የቴዎድሮስን ጽዋ ለመጎንጨት እገደድ ይሆናል::"
ከ/ል ወርቅነህ ገበየሁ

የትግራይ ብሄረሰብንም ስለማይወክሉ ሕዝባዊ መሠረት የላቸውምና መጨረሻቸው የከፋ ብቻ ሳይሆን አሳፋሪም ነው የሚሆነው:: ወያኔዎች ያልጠበቁት እረድኤት እጃቸው ስለገባ ይህንን ላለማጣት የማይሠሩት ተንኮል የለም:: ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ሕዝቡን ስለሚንቁት በሕዝቡ ጉልበትና ሀብት ሕልማቸውን ዕውን ለማድረግ እየጣሩ ነው:: ካልተሳካላቸው እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ስለሆነ ዓላማቸው ሕዝቡን ከፋፍለው እርስ በእርሱ በማዋጋት አናክሰውና ዘርፈው ሲያበቁ ለመሸሽ ነው:: የትግራይንም ሕዝብ ምንም በማያውቀው ጉዳይ ከቀሪው ወገኑ አጣልተው የቂም በቀል መወጫ ለማድረግ ነው:: ሕዝባችን አስተዋይና ታጋሽ በመሆኑ ለዚህ ፀረ-ሕዝብ ደባቸው እንደማይበገርና መሣሪያ እንደማይሆንላቸው ምርቱን ከግርዱ አንጠርጥሮ እንደሚያወጣ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታጋሽ ነው፤ ቂመኛ ባይሆንም የተሠራበትን ግፍና በደል ግን አይረሳም፤ ይቅር ባይም ነው:: ከዚህ ሕዝብ አብራክ የተገኙት የወያኔ መሪዎች በአገሪቱ ላይ እያደረሱ ያሉት ጥፋት እጅግ አስከፊና አሳፋሪ ሲሆን የትግራይ አባቶች በጠላት ወረራ ወቅት የአገርን ሉዓላዊነት ላለማስደፈር የከፈሉት መስዋዕትነት ጋር ሲነፃጸር የወላጆቻቸውን አኩሪ ታሪክ ሆን ብለው አረም እያበቀሉበት መሆኑን እንገነዘባለን::

በቅርቡም የትግራይ ክልል በሻዕብያ ሲወረር ከአራቱም ማዕዘናት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር በመንቀሳቀስ አገሬ ወገኔ ተደፈረ፤ ተጠቃ ብሎ በመዝመት አለኝታነቱን በተግባር አሳይቷል:: የተወረረውን ግዛት አስመልሶ የአገሩን ሉዓላዊነት አረጋግጧል::ገበሬው፥ ነጋዴው በጉልበቱም በገንዘቡም ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል:: ይህ ድጋፍና ትብብር በወያኔ መሪዎች ዘንድ ዋጋ ካለመሰጠቱም በላይ የቀድሞው የመከላከያ ሠራዊት የፈጸመውን ጀብዱ እንደ ቅጥረኛ ወታደር አገልግሎት በመቁጠር ሠራዊቱን ያለአንዳች ቀለብና የሥራ ዋስትና ወደየመጣበት እንዲመለስ አድርገውታል እያደረጉም ነው:: እነሱ በፈጠሩት ጣጣ በሕዝቡ ላይ ለደረሰው ጉዳት በመካስ ፋንታ ከበፊቱ በከፋ ሁኔታ ያሰቃዩታል:: ይህንን አረመኔያዊ ተግባር የትግራይ ሕብረተሰብ እንዴት ይመለከተዋል? የክልሉን ልማት ብቻ ይመለከታል ወይስ የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር በማስቀደም ይረዳል? ከአብራኩ የተወለዱ የወያኔ መሪዎች የፖለቲካና የኢኮኖሚውን ሥልጣን ለብቻቸው ይዘው 57 ሚሊዮን ሕዝብ የኩበት ጢስ ባፈነው፥ ተባይና በሽታ በመላበት ጎጆ ውስጥ ተኮራምቶ እየኖረ በረሃብ ሲያልቅ በቸልታ ከተመለከተ የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ አያምንም ለማለት ያስደፍራል:: የእሱ ልጆች የተነሱት ኢትዮጵያን ለማጥፋት ስለሆነ ኢትዮጵያ ከጠፋች መግቢያው የት ይሆን? ከኤርትራውያን ስህተት በቂ ትምህርት አላገኘንም? ነገ የሚደርስብንን እልቂትና ደም መፋሰስ ለማገድ የሚችለው የትግራይ ሕዝብ ብቻ ስለሆነ ያ ክፉ ቀን ሳይመጣ ቢያስቡበት ሁላችንም ከጥፋት ለመዳን ስለምንችል ይህንን እርምጃ አስተዋዩ የትግራይ ብሄረሰብ እንዲወስድ ከወዲሁ እማጸናለሁ::

አርማችን፤ ጥያቄያችንን ከማጠቃለላችን በፊት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማስተላለፍ የሚፈልጉት ተጨማሪ መልዕክት ካለ?

አቶ ጌታቸው፤ አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም እንደሚባለው የህገሬ ምሳሌ ሕዝባችን ሁሉንም እያየ እየሰማ ዝም ስለአለ ምን እንደምለው ይቸግረኛል:: እነዚሁ የቤት ውስጥ ጠላቶች ከመምጣቸው በፊት የነበረው ኑሮ አስደሳች ባይሆንም በአለፉት ዘጠኝ ዓመታት በደረሰበት ግፍና በደል ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ስለሚያውቀው እኔ በተጨማሪ ተጎድተሃል ብለው "ለቀባሪ አረዱት" ይሆንብኛል:: ጎረቤት ሲነካ አለሁልህ ይል የነበረ ሕዝብ ዛሬ እንደአገልጋይ ተሸቆጥቁጦ መኖርን ከመረጠ ውርደትና ንቀትን፤ ግፍና